## የፈውስ  ጸሎት

**እነሆ ፈውስ እና መድሃኒት አመጣላታለሁ፤ እፈውሳቸውማለሁ የሰላምንና የእውነትን ብዛት እገልጥላቸዋለሁ፡፡**
**ትንቢተ ኤርምያስ 33፡6**

እግዚያብሄር ይባርካችሁ! እዚህ ቦታ ላይ በህይወቴ ውስጥ ለመጸለይ የምጠቀምባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አሰባስቤ አስቀምጫለሁ፡፡ ለመጀመርያ ጊዜ የጡት ካንሰር እንዳለብኝ ሳውቅ፤ (ሙሉ ቀን ካለቀስኩ በኋላ) እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ልክ እንደመድሃኒት ለመውሰድ ወሰንኩ፡፡ ህክምናውን በምከታተልበት ወቅት፤ ሀኪሜ ለካንሰሩ መድሃኒት ሲያዝልኝ፤ ልክ በታዘዘው መሰረት ነበር መድሃኒቱን የምወስደው፡፡

መዝሙረ ዳዊት 107፡20 ላይ እግዚያብሄር ሊፈውሰን እና ከጥፋታችንም ሊያድነን ቃሉን እንደላከ ይነግረናል፡፡ ስለዚህ እግዚያብሄር ቃሉን ሊፈውሰን እና ሊያድነን ከላከ እኔም ይሄን ቃል ለእራሴ ፈውስ ለመጠቀም በልቤ ወሰንኩ፡፡ ልክ እንደመድሃኒት፤ በቀን ሶስት ጊዜ ቃሉን መውሰድ ጀመርኩ፡፡ ይሄንን ቃል ድምጼን ከፍ አድርጌ በመናገሬ መለኮታዊ የሆነው እግዚያብሄር ሀይል በውስጤ የነበረውን ካንስር እንደሚያጠፋው እጠባበቅ ነበር፡፡ እግዚያብሄር የተባረከ ይሁን ከካንሰር ጋር የነበረኝ መከራ አሁን አብቅቷል፡፡

**ስለዚህ እናንተም እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ልክ እንደ መድሃኒት እንድትጠቀሙባቸው ላበረታታችሁ እወዳለሁ፡፡** እነዚህ ጥቅሶች ለአማኞች ልክ እንደ (በገልዓድ የሚቀባ) መድሃኒት ናቸው፡፡ የእግዚያብሄር ቃል በህይወታችን እንዲሰራ መጸለይ እና ማመን ብቻ ነው ከእኛ የሚጠበቀው፡፡ ትንቢተ ኤርምያስ 1፡12 ላይ እግዚያብሄር የተናገረውን ቃል ለመፈጸም እንደሚተጋ ይነግረናል፡፡ ስለዚህ ቃሉን በእምነት እና በድፍረት እየተናገራችሁ በህይወታችሁ ሲሰራ እዩት፡፡

እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ከፍ ባለ ድምጽ መጸለያችሁ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ መዝሙረ ዳዊት145፡18 ላይ እግዚያብሄርን ለሚጠሩት ሁሉ በእውነት ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው ይላል እዚህ ጋር ለሚጠሩት ሲል ከፍ ባለ ድምጽ ለሚጠሩት ማለቱ ነው፡፡ እንደአማኞች ስንጸልይ ከፍ ባለ ድምጽ እንጸልያለን፤ ስለዚህ ቃሉንም ከፍ ባለ ድምጽ እየተናገርን እንጸልይ፡፡

በመጨረሻም፤ እምነት ይኑራችሁ፡፡ የእግዚያብሄር ልጆች እንደመሆናችሁ እርሱ ስለእናንተ እንደሚያስብ እመኑ፡፡ ለእርሱ ካላችሁ መውደድ የተነሳ ስሙን አክብሩ፡፡ ሊያድነን፤ ጸሎታችንን ሊመልስ፤ ከመከራ ለታደገን፤ሊያከብረን፤ ለጅም እድሜ ሊያጠግበን፤ ማዳኑን ሊያሳየን ቃል ገብቶልናል፡፡ እንዴት ድንቅ አምላክ ነው እኛ የምናመልከው!

እግዚያብሄር ይባርካችሁ!

## የሀኪም ትእዛዝ ስለ ፈውስ የእግዚያብሄርን ፈቃድ መጸለይ(በቀን 3 ጊዜ)

*ሀኪም ኢየሱስ*

*የማለዳ ጸሎት፡*

1. ***ጥቅስ፡ ትንቢተ ኢሳያስ 41፤10-14***
   *እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ አበረታሃለሁ እረዳህማለሁ፤ በጽድቁም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ፤ እነሆ የሚቆጡህ ሁሉ ያፍራሉ ይዋረዱማል የሚከራከሩህም እንዳልነበሩ ይሆናሉ ይጠፉማል፤ የሚያጣሉህንም ትሸሻቸዋለህ አታገኛቸውም፤ የሚዋጉህም እንዳልነበሩ እና እንደምናምን ይሆናሉ፡፡ እኔ አምላክህ እግዚያብሄር፡- አትፍራ እረዳሃለሁ ብዬ ቀኝህን እይዛለሁና፡፡ አንተ ትልቅ ያዕቆብ የእስራኤልም ሰዎች ሆይ አትፍሩ እረዳሃለሁ ይላል እግዚያብሄር የሚቤዥህም የእስራኤል ቅዱስ ነው፡፡*

   ***ጸሎት፡*** *እግዚያብሄር ከእኔ ጋር ስለሆነ አልፈራም፤ እግዚያብሄር አምላኬ ስለሆነ አልረበሽም **(ፍርሃትና መረበሽ በውስጣችሁ ካለ ለእግዚያብሄር በግልጽ ንገሩት ከዛም ላለመፍራት በልባችሁ ወስኑ፤ መንፈስ ቅዱስም ያላችሁበትን ፍርሃት እና በረበሽ ወደ እግዚያብሄር ላይ መተማመን፤ ሰላም እና ደስታ መቀየር እንደሚችል እመኑ)** እግዚያብሄር ይደግፈኛል ያግዘኛል በቀኝ እጁም ይይዘኛል፡፡ ይሄ በሽታ በፊቴ ይዋረዳል የጠላት ፍላፃ ሁሉ ይከሽፋል፡፡ እግዚያብሄር ከእኔ ጋር ስለሆነ በቀኝ እጁም ስለያዘኝ ስለሚረዳኝ እኔም ስለማምነው አልፈራም፡፡*

2. ***ጥቅስ፡ ትንቢተ ኢሳያስ 53፤4-5***
   *በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ህመማችንንም ተሸከመ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚያብሄርም እንደተቀሰፈ እንደተቸገረም ቆጠርነው፡፡ እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ ስለበደላችንም ደቀቀ የደህንነታችንም ተግሳጽ እርሱ ላይ ነበረ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን፡፡*

   ***ጸሎት፡*** *ኢየሱስ ክርስቶስ ህመሜንና በሽታዬን ተሸክሞ የሃጥያቴን ዋጋ ከፍሎልኛል፡፡ ስለ እኔ በደል ተወግቶ ስለ ሀጥያቴ ደቋል ኢየሱስ እኔ ንጹህ እንድሆን ተደብድቧል እኔ እንድፈወስ ተገርፏል፡፡ ይህ ለእኔ የከፈለውን የእርሱ የመስዋእትነት ዋጋ የሆነውን ፈውስ እቀበላለሁ፡፡*

3. ***ጥቅስ፡ ትንቢተ ኤርምያስ 1፡2***
   *እግዚያብሄርም፡- እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁ መልካም አይተሃል አለኝ፡፡*

   ***ጸሎት***፡ *የእግዚያብሄር ቃል በህይወቴ እንደሚሰራ አየጠበኩ እና እንደሚፈውሰኝ እያመንኩ ቃሉን መናገሬን እቀጥላለሁ፡፡*

4. **ጥቅስ፡ የማቴዎስ ወንጌል 21፤21-22**
   *ኢየሱስም መልሶ እውነት እላችኋለሁ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩም በበለሲቱ እንደሆነባት ብቻ አታደርጉም ነገር ግን ይህን ተራራ ተነቀለህ ወደ ባህር ተወርወር ብትሉት ይሆናል፤ አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ አላቸው፡፡*

   **ጸሎት፡** *ዛሬ፤ በሰውነቴ ላይ ያለውን ህመም እናገረዋለሁ (የህመማችሁን ስም) በጌታ በኢየሱስ ስም እዝሃለሁ ከስርህ ተነቀለህ ጥፋ ሁኑኑ ከሰውነቴ ወጥተህ ሂድ፡፡ አሁን የጸለየኩት በሰውነቴ ላይ እንደሚሆን አምናለሁ፡፡ በጌታ በኢየሱስ ስም፡፡*

5. **ጥቅስ፡ የማርቆስ ወንጌል 11፤22-26**
   *ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው በእግዚያብሄር እመኑ፡፡ እውነት እላችኋለሁ ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን በልቡ ሳይጠራጠር ይሁንን ተራራ ተነቀለህ ወደባህር ተወርወር ቢል የሆንለታል፡፡ስለዚህ አላችኋለሁ የጸለያችሁትን የለመናችሁትን ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ የሆንላችሁማል፡፡ ለጸሎትም በቆማችሁ ጊዜ በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ሀጥያታችሁን ይቅር እንዲላችሁ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት፡፡ እናንተ ግን ይቅር ባትሉ በሰማያት ያለው አባታችሁም ሀጥያታችሁን ይቅር አይላችሁም፡፡*

**ጸሎት፡** አባት ሆይ መመርያ እንደሰጠኸኝ ያሳዘኑኝን እና የጎዱኝን ሰዎች ይቅር ለማለት ወስኛለሁ(የሰዎቹ ስም) መንፈስ ቅዱስ ሆይ እባክህ ሌላ ይቅር ማለት ያለብኝ ሰው ካለ አስታውሰኝ (**መንፈስቅዱስ እንደመራችሁ ወደውስጣችሁ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ ይቅር በሏቸው ይህንንም መንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ ያለውን ቁስል እና ጠባሳ ሁሉ እንደሚያድነው እያመናችሁ ከልባችሁ አድርጉት ተጨማሪ ክርስትያናዊ ምክር የሚስፈልጋችሁ ከሆነ ማማከር ያለባችሁን ሰው አማክሩ፡፡ ደግሞም መንፈስ ቅዱስ እነደመራችሁ ይቅር ያላችኋቸውን ሰዎች አናግሯቸው ይቅርታ እነዳረጋችሁላችውም ንገሯቸው በተጨማሪም ይቅርታ መጠየቅ ያለባችሁ ሰው ካለ እነርሱንም ይቅርታ ጠይቁ ይህን ሁሉ ስታደርጉ መንፈስ ቅዱስ ይረዳችኋል መንገዱንም ያሳያችኋል ምክንያቱም የክርስቶስ የማዳን ስራ ይቅር እነድንልና ይቅር እንድንባል ነው፡፡ አስታውሱ ከሁሉም በላይ ሃጥያተኞች ሳለን ነው እግዚያብሄር እኛን ይቅር ያለን ስለዚህ እኛም ሌሎችን ይቅር ማለት መቻል አለብን፡፡ ሌሎችን ይቅር ስለማለት ከጸለይን በኋላ ስለ ፈውሳችን እንጸልይ፡፡**)

6. **ጥቅስ፡ *ወደ ሮሜ ሰዎች* 4፡17**
ለብዙ አሕዛብ አባት አደረኩህ ተብሎ እንደተጻፈ ለሙታን ህይወት በሚሰጥ የሌለውንም እነዳለ አድርጎ በሚጠራ ባመነበት በእምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው፡፡

**ጸሎት፡** እንደ አብርሃም ልጅነቴ፤ ለእርሱ የተሰጡትን የተስፋ ቃላቶች ሁሉ እቀበላለሁ ፈውስን ጨምሮ፡፡ የእግዚያብሄር ልጅ እንደመሆኔ እና እርሱን ለመምሰል እንደመጠራቴ፤ አሁን የሌሉትን እና የማየታዩትን ንገሮች እንዳሉ አድርጌ እጠራለሁ ፈውስን በሰውነቴ ላይ አዛለሁ፡፡ ዛሬ እግዚያብሄር የሰጠኝን የፈውስ ተስፋ ቃል አልጠራጠርም ነገር ግን እግዚያብሄር ሙሉ ለሙሉ እንደሚፈውሰኝ አውቄ በእምነት እቆማለሁ፡፡ ስለ መልካምነቱ እና ስለ ታማኝነቱ ለእግዚያብሄር ክብርን እየሰጠሁ በእምት እራመዳለሁ፡፡

7. **ጥቅስ፡ *ወደ ሮሜ ሰዎች* 8፡11**
ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ህይወትን ይሰጣል፡፡

**ጸሎት፡** ዛሬ፤ የእግዚያብሄርን መንፈስ አውጃለሁ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው መንፈስ ዛሬም በእኔ ውስጥ ይኖራል፡፡ በውስጤ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ በሰውነቴ ውስጥ በሽታ እያጠቃው ያለውን አካሌን ህይወትን እነደሚሰጠው አምናለሁ፡፡ ሰውነቴ ሆይ፡- በእኔ ውስጥ ካለው ህይውት ሰጪ የሆነው የእግዚያብሄር መንፈስ የተነሳ ተፈውሰሃል፡፡

**የቀትር ጸሎት**

8. **ጥቅስ፡ *ወደ ሮሜ ሰዎች* 8፡12-14**
እንግዲህ ወንድሞች ሆይ እዳ አለብን እንደስጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለስጋ አይደለም፡፡እንደስጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና በመንፈስ ግን የሰውነትን ስራ ብትገድሉ በህይወት ትኖራላችሁ፡፡ በእግዚያብሄር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚያብሄር ልጆች ናቸውና፡፡

**ጸሎት፡** እኔ የእግዚያብሄር ልጅ ነኝ ስለዚህ ህይወቴን እንዲመራ ፈቃድ የሰጠሁትና ህይወቴንም እየመራ ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

9. **ጥቅስ፡ *ወደ ሮሜ ሰዎች* 8፡15-17**
አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እነጂ እነደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና የእግዚያብሄር ልጆች መሆናችንን ያመንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን ማለት የእግዚያብሄር ወራሾች ነን አብረንም ደግሞ እንድንከብር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን፡፡

**ጸሎት፡** በክርስቶስ የተቀበልኩት የፍርሃት መንፈስን ሳይሆን የእግዚያብሄርን መንፈስ ነው፡፡ እግዚያብሄር አባቴ ነው፤ ከልጆቹ አንዱ በመሆኔ የወራሽነት መብት አለኝ በእኔ ውስጥ ከሚኖረው ከክርስቶስ የተነሳ የክብሩ ወራሽ ነኝ ይህ ክብር ፈውሴን ያካትታል እኔም ተቀብዬዋለሁ፡፡ ከእግዚያብሄር ከተቀበልኩት ክብር የተነሳ የክርስቶስን ወንጌል ለቤተሰቤ፤ ለስራ

ባልደረቦቼ፤ለጓደኞቼ፤ለማገኘውሰው ሁሉ እመሰክራለሁ፡፡ ከእግዚያብሄር ክብር ስካፈል ከስቃዩም እንደምካፈል አውቃለሁ ይህንንም በማደርግበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚረዳኝ አምናለሁ፡፡

*10.* **ጥቅስ፡ 2 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 10፡ 3-5**
በሰው ልማድ ምንም እንኳን ምንመላለስ ብንሆን እነደሰው ልማድ እንዋጋም የጦር አቃችን ስጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚያብሄር ፊት ብርቱ ነው የሰውንም ሃሳብ በእግዚያብሄርም እውቀት ላይ የሚነሳውን ከፍ ያለን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፡፡

**ጸሎት፡** ሰው እንደመሆኔ ሌሎች ሰዎች ህመምን በሚዋጉበት መንገድ ህመሜን አልዋጋም ነገር ግን ብርቱ የሆነውን የእግዚያብሄርን ቃል ተጠቅሜ ሊያስፈራራኝ እና ጥርጣሬ ውስጤ ሊያስገባ የሚሞክረውን ነገር ሁሉ አሸንፋለሁ፡፡ የህንን ብርቱ የሆነውን የእግዚያብሄርን ቃል ማንኛውንም የእግዚያብሄር የተስፋ ቃላቶች በህይወቴ እንዳልመሰክር የሚያግደኝን ውሸት አፈርስበታለሁ፡፡ ውስጤ ያለውን ማንኛውንም የኩራትና ያለመታዘዝ መንፈስ አውጥቼ እግዚያብሄርን መታዘዝ ራሴን አስተምራለሁ እግዚያብሄርን እንደፈዋሽ አምላክ ብቻ ሳይሆን እንደ አባት፤ ወንድም፤ አጽናኝ፤ አስተማሪ ሁሉነገር መሆኑን ለመረዳት ልቤን እከፍታለሁ፡፡

11. **ጥቅስ፡ ወደ ገላትያ ሰዎች 3፡13-14**
በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ ተረገመ ነው ተብሎ ተጸፏልና ክርስቶስ ስለኛ እርግማን ሆኖ ከህግ እርግማን ዋጀን የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድቀበል የአብርሃም በረከት ወደ አህዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ፡፡

**ጸሎት፡** በኢየሱስ ክርስቶስ ድኛለሁ ስለዚህም ከዚህ በሽታ ነፃ ነኝ በህግ እርግማን ውስጥ አልኖርም በህመም እርግማን ውስጥ አልኖርም እንደተፈወስኩ፤ ሙሉ ለሙሉ ነፃ እንደሆንኩ አውቃለሁ፡፡ እግዚያብሄር አብርሃምን በጤንነት እና በሙላት እንደባረከው እኔም በረከቱን እወስዳለሁ፡፡

12. **ጥቅስ፡ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6፡10-16**
በቀረውስ በጌታና በሀይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ፡፡ የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚያብሄርን እቃ ጦር ሁሉ ልበሱ፡፡ መጋደላችን ከደምና ከስጋ ጋር አያደለምና ከአለቆች እና ከስልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ አለም ገዢዎች ጋር በሰማያዊውም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳዊያን ሰራዊት ጋር ነው እንጂ፡፡ ስለዚህ በክፉ ቀን ለመቃወም ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚያብሄርን እቃ ጦር ሁሉ አንሱ፡፡ **እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፡፡** በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉ ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ  የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሱ፡፡

**ጸሎት፡** ከእግዚያብሄር ሀይል እና ብርታት የተነሳ ጠንካራ ሰው ነኝ ይሄንን ህመም ሆነ ማንኛውንም የጠላት ስራ እቋቋማለሁ ከስጋ ስሜት እና ፍላጎት ጋር አልታገልም በእግዚያብሄር ቃል ተደግፌ ከዚህ ምድር ሃይላትና ስልጣናት ጋር ነው የምዋጋው በመጨረሻም አሸንፋለሁ፡፡
ስለዚህ ወገቤን እውነት በሆነው የእግዚያብሄር ቃል እታጠቃለሁ ቃሉን ቀን እና ሌሊት በፊቴ አደርጋለሁ፤ እምነቴን እሴቶቼን እና ስሜቴን ለመጠበቅ የጽድቅን ጠሩር አለብሳለሁ፤ በዚህ መከራ ውስጥ እያለፍኩ ቢሆንም ሁልጊዜ መልካም እና ሰላማዊ የሆነውን ነገር ለማድረግ እመርጣለሁ፡፡ እግዚያብሄር ሆይ በህይወቴ ማስተካከል ያለብኝ ነገር ካለ በመንፈስህ ማስታወስ እና ማስተካከል እንድችል አርዳኝ፡፡ ምንም ያህል ድካም እና ህመም ቢሰማኝም እግዚያብሄር እንደሚፈውሰኝ አምናለሁ የእግዚያብሄር ቃል ሰውነቴን እየፈወሰው ነው ተፈውሻለሁ፡፡

13. **ጥቅስ፡ ወደ ፊሊጵስዩስ ሰዎች 1፡6**
በእናንተ መልካምን ስራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቻለሁና፡፡

**ጸሎት፡** ስራውን በእኔ የጀመረ እግዚያብሄር እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ መምጫ ድረስ እነደሚጨርሰው አምናለሁ፡፡

14. **ጥቅስ፡ወደ ፊሊጵስዮስ ሰዎች 2፡13**
ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሰራ እግዚያብሄር ነውና፡፡

**ጸሎት፡** እግዚያብሄር በቃሉ በእኔ ውስጥ እየሰራ እነደሆን እና በልቤ ያለውን እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ለመዳን የለኝን ፍላጎት እርሱ እንደሰጠኝ አምናለሁ፡፡

**የምሽት ጸሎት**

15. **ጥቅስ፡ ወደ እብራውያን 10፡19-23**
እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በመረቀልን በአዲስና በህያው መንገድ ወደቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በስጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን በእግዚያብሄርም ቤት ላይ የሁሉ ታላቅ ካህን ስላለን ከክፉ ህሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውሃ ታጥበን በተረዳነበት እምነት በቅን ልብ እረቅረብ የተስፋን ቃል ሰጠው የታመነ ነውና እንዳይነቃነቅ ተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ፡፡

**ጸሎት፡** በክርስቶስ ኢየሱስ ሙሉ ለሙሉ እንደ ተፈወስኩ በእግዚያብሄር ላይ እምነት አለኝ ህሊናዬ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ስለፀዳ ምንም አይነት የሀጥያት ውንጀላ የለብኝም፡፡ አዲስ ሰው ነኝ ሰውነቴም በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ንጹህ ነው፡፡

16. **ጥቅስ፡ወደ እብራውያን 10፡35-39**
እንግዲህ ታላቅ ብድራት ያለውን ድፍረታችሁን አትጣሉ የእግዚያብሄርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችሃልና፡፡ **ገና በጣም ጥቂት ጊዜ ነው ሊመጣ ያለውም ይመጣል አይዘገይምም ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል ወደኋላም ቢያፈገፍግ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም፡፡** እኛ ግን ነፍሳቸውንን ሊያድኑ ከሚያምኑት ነን እንጂ ወደጠፉት ከሚያፈገፍጉት አይደለንም፡፡

**ጸሎት፡** እምነቴ ሙሉ ለሙሉ በእግዚያብሄር ላይ ነው ሰውነቴም ሙሉ ለሙሉ ይፈወሳል ስለዚህ ለአምሮዬ፤ ለስጋዬ፤ ለነፍሴ እና ለመንፈሴ እናገራለሁ እግዚያብሄርን በትእግስት ተጠባበቁ እንደጻድቅ ሰው በእምነት እኖራለሁ ሙሉ ለሙሉ ተፈውሻለሁ፡፡

17. **ጥቅስ፡ወደ እብራውያን 11፡11-12 እና 13፡8**
ተስፋ የሰጠው የተታመነ እንደሆነ ስለቆጠረች ሳራ ራስዋ ደግሞ ዕድሜዋ እንኳ ካለፈ በኋላ ዘርን ለመፀነስ ሀይልን በእምነትን አገኘች፡፡ **ስለዚህ ደግሞ በብዛታቸው እንደ ሰማይ ኮከብ እነደ ማይቆጠር በባህር ዳር እንዳለ አሸዋ የበዙት** የሞተን ሰው እንኳ ከመሰለው ከእንዱ ተወለዱ፡፡
ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለም ህያው ነው፡፡

**ጸሎት፡** ለፈውሴ በእምነት ጸንቼ አቆማለሁ ኢየሱስ አንተ ትናንት ዛሬም ነገም ለዘላለም ያው ነህ ስለዚህ የሞተውን የሳራን ማህጸን ሕያው ያደረክ በልጅም የባረካት ያለምንም ጥርጣሬ የእኔንም ህመም ማጥፋት እንደምትችል አምናለሁ በውስጤ ካለው መንፈስህ የተነሳ ተፈውሻለሁ ሰውነቴ፤ በጌታ በኢሱስ ክርስቶስ ስም ተፈወስ፡፡

18. **ጥቅስ፡ የያዕቆብ መልእክት 5፡14**
ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተክርስትያንን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ሰም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት፡፡

**ጸሎት፡** ለዚህ ጥቅስ የሚለውን አድርጉ በእግዚያብሄር የበረታ እምነት ያለው ለህማችሁ በእምነት ሊጸልይ የሚችል ሰው ፈልጋችሁ በዘይት ቀብቶ ይጸልየላችሁ፡፡ በተጨማሪም ንሰሃ መግባት ያለባችሁ ነገር አነዳለ ከተሰማችሁ የመጀመርያው የዩሐንስ መልእክት 1፡9 ላይ እነደሚለው እግዚያብሄር ሀጥያታችሁን የቅር እናደሚል አምናችሁ ንሰሃ ግቡ፡፡

19. **ጥቅስ፡ 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2፡24**
ለሐጥያት ሞተን ለጽድቅ እነድንኖር እርሱ ራሱ በስጋው ሐጥያታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፡፡

**ጸሎት፡** ኢየሱስ ክርስቶስ ሀጥያቴን በመስቀል ላይ ተሸክሞልኛል ለሀጥያት ሞቻለሁ ለጽድቅ አኖራለሁ በእርሱ ቁስል ተፈውሻለሁ፡፡

20. **ጥቅስ፡ 1ኛ የዩሐንስ መልእክት 5፡14**
በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል፡፡

**ጸሎት፡** እግዚያብሄር ጸሎቴን እንደሰማኝ እርግጠኛ ነኝ ምክንያቱም የእርሱ ፈቃድ የሆነውን ቃሉን ነው የጸለይኩት እንደሰማኝ ስለማውቅም ተፈውሻለሁ፡፡

21. **ጥቅስ፡ የየሐንስ ራእይ 12፡10-11**
ታላቅም ድምጽ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል አሁን ያምላካችን ማዳንና ሀይል መንግስትም የክርስቶስም ስልጣን ሆን ቀንና ሌሊትም በእምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሏልና፡፡

**ጸሎት፡** ሰይጣን በክርስቶስ ኢየሱስ ደም እንደተሸነፈ እና እኔም እንደተፈውስኩኝ አውቃለሁ የእኔ ምስክርነት እንደተፈወስኩ ነው እንደተፈወስኩ የማያምኑ ሰዎች አያስፈሩኝም፡፡ በተጨማሪም የእግዚያብሄርን መልካምነት እና በህይወቴ ያየሁትን የእርሱን በረከት ለሁሉም እናገራለሁ፡፡ የጠላት ስራ ሁሉ በሰውነቴ ላይ ያቀደው ነገር ሁሉ ፈርሷል፡፡

የሀኪም ኢየሱስ መድሃኒት ማዘዣ እዚህ ጋር ያበቃል